# FORUM FOR SOCIAL STUDIES

## CIVIL SOCIETY AND ENVIRONMENTAL POLICY DIALOGUE



*CONSULTATION PAPERS ON ENVIRONMENT No. 6*

የግልና የጋራ ጥረት ለአካባቢ ሕይወት መሻሻል
(የሰሜን ሸዋ ገበሬዎች ተሞክሮ)

**Addis Ababa**
**May 2004**

# FORUM FOR SOCIAL STUDIES

# CIVIL SOCIETY AND ENVIRONMENTAL POLICY DIALOGUE

## CONSULTATION PAPERS ON ENVIRONMENT No. 6

## የግልና የጋራ ጥረት ለአካባቢ ሕይወት መሻሻል
## (የሰሜን ሸዋ ገበሬዎች ተሞክሮ)

**Addis Ababa**
**May 2004**

©2004 Forum for Social Studies and the Authors.
Report Pepared by Girma Feyissa
Cover Photos: FSS
Camera Ready Copy: Prepared by Mihret Demissew

# ማ ው ጫ

ገጽ

1. የመክፈቻ ንግግር ........ 1

2. የአንኮበር (ሰሜን ሸዋ) በገሬዎች ስለተሞክሯቸው
ስብሰባው ላይ ያደረጉት ገለፃ ........ 5

3. የቪዲዮ ፊልም ትዕይንት ........ 9

4. የጽዱና አረንጓዴ አዲስ አበባ እንቅስቃሴ ........ 10

5. የት/ቤቶች የአካባቢ ጥበቃና እንክብካቤ ክበባት እንቅስቃሴ ........ 11

6. የአዲስ አበባ የጽዳት፣ ውበትና መናፈሻ ልማት ........ 12

7. የቤተ-ክህነት የዕፅዋት ጥበቃና እንክብካቤ ........ 12

8. የወደፊት የእንቅስቃሴ አቅጣጫ ........ 14

# የሲቪል ማኅበረሰብና የአካባቢ ፖሊሲ ውይይት

**6ኛ መድረክ፤ ህዳር 26 ቀን 1996 ዓ.ም. ግዮን ሆቴል**

## የግልና የጋራ ጥረት ለአካባቢ ሕይወት መሻሻል

በማኅበራዊ ጥናት መድረክ (ማጥመ) አማካይነት "የግልና የጋራ ጥረት ለአካባቢ ሕይወት መሻሻል" በሚል ርዕስ ህዳር 26 ቀን 1996 ዓ.ም. በግዮን ሆቴል አዋሽ አዳራሽ ውስጥ ከጧቱ 3 ሰዓት ጀምሮ ሙሉ ቀን የፈጀ ውይይት ተካሂዷል። የዕለቱ ፕሮግራም ሁለት ክፍሎች የነበሩት ሲሆን የጧቱ ክፍለ ጊዜ ውይይት ያተኮረው በገጠሩ ሁኔታ ላይ ሲሆን ከቀትር በኋላ የተካሄደው ውይይት ያተኮረው በከተማው ሁኔታ ላይ ነበር።

በፕሮግራሙ መግቢያ ላይ የማኅበራዊ ጥናት መድረክ (ማጥመ) ሥራ አስኪያጅ አቶ ደሳለኝ ራህማቶ ባደረጉት አጭር የእንኳን ደህና መጣችሁ ንግግር ተሳታፊዎቹ ጥሪያቸውን አክብረው ትምህርታዊ በሆነውና ሀገራዊ ጠቀሜታ ባለው ርዕስ ላይ ውይይት ለማድረግ በመገኘታቸው የተሰማቸውን ደስታ በድርጅታቸውና በራሳቸው ስም ገልጠዋል። ይልቁንም የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ዋና ሥራ አስኪያጅ ዶክተር ተወልደ ገብረ እግዚአብሔር ጥሪውን አክብረው የመክፈቻ ንግግር ለማድረግ በመፍቀዳቸውና የዕለቱን ውይይት ልዩና ብርቅ ያደረገው ከሰሜን ሸዋ ከአንኮበር ድረስ ረዥም መንገድ ተጉዘው ልምዳቸውን ለማካፈል በስብሰባው ላይ መገኘት መሆኑን ገልፀው አራቱ ገበሬዎች ላሳዩት ልዩ ትብብር ልባዊ ምሥጋና አቅርበዋል።

በመቀጠልም ይህ የገጠርና የተለያዩ የከተማ ኅብረተሰብ ክፍሎች የሚሳተፉበት ጉባዔ ዋና ትኩረት በአካባቢ ጥበቃና እንክብካቤ ተግባር የሕዝብ ተነሳሽነትና ተሳትፎ ምን ያህል አመርቂ ውጤት ሊያመጣ እንደሚችል ግንዛቤ የሚያስጨብጥ መሆኑን ገልጸው የፕሮግራሙን አስተባባሪ አቶ ግርማ ሀይሉንና



ስብሰባውን በየተራ በሊቀመንበርነት ለመምራት ፈቃደኛ የሆኑትን አቶ ጌታቸው እሸቴና አቶ ረጋሳ ፈይሳን ስለ ትብብራቸው ከልብ ካመሰገኑ በኋላ የዕለቱን ፕሮግራም አስተዋውቀው ወደ ሥፍራቸው ተመልሰዋል።

በመቀጠልም የፕሮግራሙ አስተባባሪ አቶ ግርማ ሃይሉ አጭር የመግቢያ ንግግር አድርገዋል። በዚሁ ንግግራቸው የማኅበራዊ ጥናት መድረክ (ማጥመ) ተሳታፊዎችን ግንዛቤ በማስጨበጥ ላይ ያተኮሩ በዛ ያሉ ስብሰባዎች በተለያዩ ርዕሶች ላይ ማዘጋጀቱን አስታውሰው የዕለቱን ስብሰባ ልዩ የሚያደርገው አካባቢያቸውን ለማሻሻል ተጨባጭ አስተዋጽኦ ያደረጉ ግለሰቦችና ድርጅቶች ስለተሞክሯቸው ለስብሰባው ለገጻ የሚያደርጉ በመሆናቸው እንደሆነ አብራርተዋል።

ባለፉት አስር ዓመታት አካባቢን የተሻለ የመኖሪያ ሥፍራ በማድረግ ላይ ያተኮሩ ልዩ ልዩ ፖሊሲዎች መነደፋቸውን አስታውሰው በነዚህ ዓመታት ልዩ ልዩ ግንዛቤዎች መዳበራቸውን ጠቅሰዋል።

አያይዘውም በአሁኑ ጊዜ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ዓቢይ ጉዳይ እነዚህን የተለያዩ አካላት እንዴት አድርገን አስተባብረንና አቀነባብረን ተግባራዊ እንቅስቃሴ ማካሄድ እንችላለን ከሚል ምዕራፍ ላይ መደረሱን አስገንዝበዋል። ይህንን ዓላማ ለማሳካት መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችና ግለሰቦች በተናጠል የሚያደርጉት እንቅስቃሴ በገንዘብ፤ በጉልበትና በሥራ ድግግሞሽ የተነሳ ከፍተኛ ሀብት የሚባክን በመሆኑ ተቀናጅቶ መሥራት እንደሚያስፈልግና ጠቃሚ እንደሆነ ጠቁመዋል።

ለረዥም ዘመን ደን ሲጨፈጨፍና መሬቱ ሲታረስ ስለቆየ በአፈር መከላት ምክንያት የሚደርሰውን አደጋ ለመከላከል ከረጅም ዘመን ጀምሮ አርሶ አደሩ በራሱ የፈጠራ ችሎታ በመጠቀም የአፈር መከላትን የመከላከያ ዘዴ አዳብሯል በማለት አድናቆታቸውን ከገለጡ በኋላ ይህንኑ ባህላዊ የአፈር ጥበቃ ልምዳቸውን ለማካፈል በገጠሩ አካባቢያቸውን ለማሻሻል ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረጉ አራት የአንኮበር (ሰሜን ሸዋ) ገበሬዎች በስብሰባው ላይ የተገኙ መሆናቸውን አስረድተዋል።

በከተማ ውስጥ የሚደረጉ ጥረቶችንም በተመለከተ ስለተሞክሯቸው ገለጻ እንዲያደርጉ ግለሰቦችና ቡድኖች መጋበዛቸውን አቶ ግርማ ካሳወቁ በኋላ የስብሰባው ዓላማ ከዚህ ቀደም የተገኙ ውጤቶችን በመገምገም ጉዳዩ የሚመለከታቸው ሁሉ ወደፊት መከተል በሚገባቸው የድርጊት መርሃ ግብር ሃሳብ ዙሪያ ለመወያየትና ሕዝብን ሊያሳትፉ በሚችሉ ፕሮግራሞች ላይ የሃሳብ ልውውጥ ለማድረግና ተግባራዊ ሊሆኑ ስለሚችሉ ዘዴዎች ለመወያየት መሆኑን አስታውቀዋል።

የመስማሚያ ሀሳቦችን መንደፍና የሚገኙ ውጤቶችን ወደፊት በሚደረጉ

ስብሰባዎች ላይ ገምግሞና አዳብሮ አባላት እንዲያውቁት ለማድረግ በሚያስችሉ ሀሳቦች ዙሪያ ሰፊ የሃሳብ ልውውጥ እንደሚያደርግም በተጨማሪ ገልጸዋል። ከዚህ አንፃር እስካሁን ድረስ የወጡ የፖሊሲ ሃሳቦች መንግሥታዊና መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች እንዲሁም በግለሰቦች ደረጃ የተደረጉትን ጥረቶች በተለይም በገጠርና በከተማ ደረጃ የተከናወኑትንና የታቀዱትን መገምገሙ ጠቃሚ ትምህርት ሊያስገኝ ስለሚችል ውይይቱ መዘጋጀቱ ጠቃሚ መሆኑን በማስገንዘብና ለዚሁም ማጥመን በማመስገን የመግቢያ ንግግራቸውን አጠቃለዋል።

ከአቶ ግርማ ሀይሉ ንግግር ቀጥሎ የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ዲሬክተር የሆኑት ዶ/ር ተወልደ ገ/እግዚአብሔር በቅድሚያ በስብሰባው ላይ የአካባቢ ጉዳይ በይበልጥ በጎ ተሳትፎና ጠቃሚ ሥራ የሚሰሩት ሴቶች ቁጥር ለወደፊቱ እንደሚበረክት ያላቸውን ተስፋ በመጠቆም ስለተደረገላቸው ጥሪ የውይይት መድረክ ያዘጋጀውን የማኅበራዊ ጥናት መድረክን (ማጥመ) ካመሰገኑ በኋላ በውይይቱ ላይ በመገኘታቸው የተሰማቸውን ደስታ ገልፀዋል። ለወደፊቱም የዚህ ዓይነት ጥረት በግልም ሆነ በጋራ እንደሚቀጥል ያላቸውን እምነት ገልጸዋል።

ቀጥለውም የአካባቢ ብክለት መከሰት ችግር በሀገራችን ለሚከሰቱ ዋና ዋና ችግሮች መንስዔ ናቸው ብለው እንደሚያምኑ በመግለጽ ምክንያቶቹን ዘርዝረው አብራርተዋል።

እነርሱም በመሬት መጎሳቆል፣ ግለሰቦችና ማህበረሰቦች በዘፈቀደ በሚጥሉት ቆሻሻ፣ በፋብሪካዎች ከግብርናና ከአገልግሎት ተቋሞች ከሚለቀቁ ዝቃጮችና የትም ከሚጣሉ ቆሻሻዎች እንደዚሁም ከህክምና ተቋማት ከሚወጡ ፍሳሾችና በግቢያቸው ከሚጣሉ ጠንቀኛ ጥራጊዎች የሚከሰቱ መሆናቸውን ገልጸዋል።

አያይዘውም ሲናገሩ ከግለሰብ፣ ከማህበረሰብና ከመንግሥት አኳያ መታየት ያለበት ትልቁ ችግር የመሬት መጎሳቆል ችግር እንደሆነና ተገቢ ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባ ተናግረዋል።

በከተሞች ከሚታዩት ችግሮች መካከል በጋራ የማቆሸሽ አዝማሚያ በተለይም ፌስታልን በመጠቀም አካባቢን በጉድፍና ቆሻሻ ማጎሳቆልን በመቋቋም ረገድ ከተማችንን በጋራ እንድናፀዳ ፈር ቀዳጅ ርምጃ በመጀመራቸው እነ ጋሽ አበራ ሞላን አድንቀዋል። በገጠር አካባቢ ቆሻሻም አይበዛም ቢኖርም ለመሬት ማዳበሪያነት እንደሚያገለግል አስረድተዋል።

ከእነዚህ ከተጠቀሱት ቆሻሻዎች በተጨማሪ ዘመናዊነትን በመሻት ምንነታቸውን የማናውቀው ከየፋብሪካው የሚወጡ ቆሻሻዎች እንዳሉም አብራርተዋል። ከዚህም በቀር ሰውን ለማዳን ከተቋቋሙ ድርጅቶችና ከሆስፒታሉ የሚወጡ ጠንቀኛ ቆሻሾች በተጨማሪ እስካሁን ዘልቀው ስር ያልሰደዱ ለወደፊት ግን

አስጊ ሁኔታ ሊፈጥሩ የሚችሉ እንደ ዘረ-ምህንድስና (Genetic Engineering) ያሉ ጠንቆችም እንዳሉ ጠቁመዋል።

እነዚህን ችግሮች ለመቋቋም ህብረተሰቡ በንቃትና በጋራ በመታገል ሀገር ከቆሻሻ እንድትጠበቅ ማድረግ የዜጎች ሁሉ ድርሻ መሆኑን አስምረውበታል። ሕብረተሰቡ ችግሩን በግልጽ የሚያውቀው ስለሆነ ተሳታፊነቱን ማበረታታት ውጤታማ ተግባር መሆኑን በመገንዘብ በስብሰባው ላይ የተገኙት የህብረተሰቡ ተወካዮች ናቸውና ለዚህ ክቡርና የተቀደሰ ዓላማ እንዲታገሉ አደራ ጭምር አሳስበዋል።

የአካባቢ ጥበቃን በተመለከተ ሶስት አዋጆች ከወጡ አንድ አመት እንዳለፈ ዶ/ር ተወልደ ገ/እግዚአብሔር አስታውሰው ለተግባራዊነቱም በቂ ዝግጅት መደረጉን ገልጸዋል። ይህ አዋጅ በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ አንድ ግለሰብ ወይም ቡድን በአካባቢ የሚከሰቱ ብክለቶችን ወይም ወደፊት ለብክለት ይዳረጋሉ ብለው የሚያምኑባቸው ጠንቀኛ ተግባሮች ለመቆጣጠር በፍርድ ቤቶች ክስ መስርተው የሕግ ጥበቃ ለማግኘት የሚያስችል አዋጅ መሆኑን አስረድተዋል። ይሁንና ወደ ክስ ከማምራት በፊት ችግሮችን በጋራ ተወያይቶ ለመፍታት መሞከር ሕዝባዊና ማህበራዊ አመለካከት የተላበሰ ሂደት ከመሆኑም በላይ ጠቃሚም እንደሆነ ያላቸውን አስተያየት አስረድተዋል።

በመጨረሻም አካባቢን ለመንከባከብ ለመጠበቅና በተቻለ አቅም የተበላሸውን አካባቢን ለማሻሻል በማህበረሰቦች፣ በህዝብ ድርጅቶች፣ በሀይማኖት ድርጅቶችና በመሳሰሉት ተቋሞች የሚደረጉ ጥረቶች ሊበረታቱ የሚገባ መሆኑን አሳስበዋል።

አንድ ሊታወቅ የሚገባው ዓቢይ ቁምነገር መኖሩን ሲጠቁሙ በገጠሩ አካባቢ ገበሬው ምንም እንደማያውቅ የመቁጠር ችግር ነው። የሚወጡትን መመሪያዎች ተግባራዊ ለማድረግ በሚወሰዱ ርምጃዎች ለምን አልተሳተፍንም ብሎ መጠየቅ እንደሚያስፈልግ አስረድተዋል። ከዚሁ ጋር በተያያዘ የመንግሥትም ኃላፊነት ማሳሰብ እንደሚያስፈልግ አብራርተዋል።

ከዚህ ጋር በተያያዘ በስብሰባው ላይ የተገኙት የተለያዩ ማህበረሰብ አባላት ስለችግሩ ግንዛቤ ጨብጠው የመግባቢያ ሀሳቦችን በመንደፍ የወደፊት የትኩረት አቅጣጫ በጋራ እንዲቀይሱ ጠቁመው ዶ/ር ተወልደ ስለአጠቃላይ የአካባቢ ጥበቃና እንክብካቤ አንገብጋቢነት በማስገንዘብ የመክፈቻ ንግግራቸውን አጠቃለዋል።

## የአንኮበር (ሰሜን ሸዋ) ገበሬዎች ስለተሞክሯቸው ስብሰባው ላይ ያደረጉት ገለጻ

የሻይ ዕረፍት ከተደረገ በኋላ በግብርናው መስክ ያካበቱትን ልምድ ለማካፈል ከአንኮበር (ሰሜን ሸዋ) የተጋበዙት ወ/ሮ አየለች ፍቅሬ፣ መምሬ ላቀው ዘውዴ አቶ ኃይለጊዮርጊስ ሳህሌና አቶ ታምሬ ሙሉነህ የተባሉት ገበሬዎች ስለተሞክሯቸው ሰፋ አድርገው አብራርተዋል። ሶስቱም ገበሬዎች አፈርና ውሃ "ሕይወታቸው" እንደሆኑ እንደሚያምኑና ለመኖር እጅግ ጠቃሚ የሆኑትን ነገሮች ለመንከባከብ ያላሰለሰ ጥረት እያደረጉ መሆናቸውን ገልጸዋል።

ወ/ሮ አየለች ፍቅሬ ባደረጉት ገለጻ ከዛሬ አርባ ዓመት ጀምሮ ለአባታቸው የገቡትን የአፈር መንከባከብ ቃል በመጠበቅና ባላቸው አቅም ሁሉ ጥረት ለማድረግ እንዲሁም በልጃቸው በሚደረግላቸው በጉልበት እርዳታ የድንጋይ ካብ በመሥራትና ጭንጫ መሬት ላይ የውሃ ማጠራቀሚያ በመቆፈር ከላይ የሚወርደውን የጎርፍ ውሃ በማቆር የውሀ መውረጃ ቦይ ሰርተው ውሃውን በመጠቀም እንዲሁም አፈሩን በመንከባከብ የተለያዩ አትክልቶችን አምርተው ተጠቃሚ ለመሆን እንደቻሉ አስረድተዋል።

በተራራው ላይ ባህር ዛፍ፣ ጌሾ፣ በደለሉ ላይ የተለያዩ የጓሮ አትክልቶች፣ ቡናና እንሰት በመትከል በሚገኘው ምርት ኑሮዋቸው መሻሻሉን በተጨማሪ አብራርተዋል። ወይዘሮ አየለች ስለ አፈር እንክብካቤ ሲናገሩ "ውሃና አፈር ህይወት ስለሆኑ አላግባብ ሲባክኑ ሳይ እንባዬ ይፈሳል። ውሃን እንደ እናቴ ጡት እጠባዋለሁ፤ አፈርን እንደ እንጀራ እጎርሰዋለሁ" በማለት ወ/ሮ አየለች ስለ ሁለቱም የተፈጥሮ ሀብቶች ያላቸውን ከፍተኛ ግምት ገልጸዋል።



ወ/ሮ አየለች ስለ ጠንክሮ መስራት ሲናገሩ የጎርፍ ውሃ አፈር እንዳይወስዳቸው በማሰብ በጠፍ ጨረቃ ጭምር እንደሚሰሩ አብራርተዋል። አያይዘውም ሲናገሩ "ሰው ይወለዳል መሬት ግን አይወለድም ስለዚህ መሬት እንዳይበርዳት ማልበስ እንዳይርባት ማጉረስ ያስፈልጋል። የብሳና ቅጠልና ሳር በመትከል አፈሩን እሸፍናለሁ ድንጋይ አጎርሳለሁ።" ሲሉ አስገንዝበዋል።

በተጨማሪም በስብሰባው የመክፈቻ ንግግሮች ላይ አስቀድሞ እንደተጠቀሰው ወትሮውንም ቢሆን የአካባቢያቸው ገበሬዎች በጋራ የመሥራት ልምድ ያላቸው መሆኑን ገልጸው በህብረት የመስራት ጠቃሚነቱን በስፋት የተገነዘቡ ስለሆነ ለወደፊቱ ይህንን የጋራ ትብብር በማጠናከር የተሻለ ውጤት ለማግኘት እንደሚጥሩ ያላቸውን ፍላጎት በመግለጽ ንግግራቸውን አጠቃለዋል።



ሁለተኛው ተናጋሪ የስልሳ አራት ዓመቱ ገበሬ መምሬ ላቀው ዘውዴ ይባላሉ። እርሳቸውም ማንነታቸውን ካስተዋወቁ በኋላ ቀደም ሲል ኑሯቸው በችግር የሚገፋ እንደነበር አስታውሰው አሁን ግን አቶ ሚሊዮን ዓለማየሁ በሚባሉ ባለሙያ በመታገዝ የተሻሻለ የግብርና ሙያ ቀስመው ከባለቤታቸውና ከልጆቻቸው ጋር በመሆን አፈር እንዳይሸረሸር የድንጋይ ካብ እርከን እየካቡ ጌሾ፣ ብሳና፣ ጽድና ባህር ዛፍ በመትከል ባለቻቸው አነስተኛ መሬት በመጠቀም ኑሮዋቸው እንደተሻሻለ ገልጸዋል። የጓሮ አትክልትን በተመለከተ ቀይ ስር፣ ካሮት፣ ጥቅል ጎመን፣ አቮካዶ፣ ፓፓዬና ማንጎ የመሳሰሉትን ፍራፍሬዎች በመትከል ከቤተሰባቸው የምግብ ፍጆታ ተርፎ ለገበያ በማቅረብ እንደሚጠቀሙ አስረድተዋል።



ሶስተኛው ተናጋሪ አቶ ኃይለጊዮርጊስ ሳህሌ ይባላሉ። አቶ ኃይለጊዮርጊስ እራሳቸውን ካስተዋወቁ በኋላ በአካባቢያቸው ያሉትን ገበሬዎች በመወከል በስብሰባው ላይ ለመገኘት

በመቻላቸው ፈጣሪያቸውን አመስግነዋል። በመቀጠልም በአንድ አካባቢ ያለን አፈር አጥፊውም አልሚውም የአካባቢው ነዋሪ መሆኑን ገልጸው አፈሩ በዝናብ ታጥቦ ሲወሰድ ዝም ብሎ ማየት በአጥፊነት የሚያስፈርጅ ሲሆን በቅጠልም ሆነ በድንጋይ በመክበብ የአፈር መሸርሸር እንዳይከሰት አድርጎ በጥቅም ላይ ማዋል የልማት አስተዋጽኦ እንደሆነ ያላቸውን እምነት አስረደተዋል። በመቀጠልም እራሳቸው በሚኖሩበት ወርጭቅንብል በምትባል አረሃማ አካባቢ የሰፈሩት በንጉሥ ኃይለሥላሴ ዘመን መሆኑን ገልጸው የራሳቸውንና የቤተሰባቸውን ሕይወት ለመታደግ ባደረጉት ጥረት ውሃና አፈር ከሌለ ህይወት እንደሌለ ባላቸው እምነት ዝናብ ሲዘንብ ጃንጥላና ወስከምባይ እራሳቸው ላይ በመድፋት አፈሩን እንደሚጠብቁ ገልጸዋል። ሆኖም ቀደም ባለው ጊዜ ምንም ያህል ጥረት ቢያደርጉም ትምህርት ስለሌላቸው ለረሃብ መጋለጣቸውን አስታውሰው አሁን ግን መንግሥታዊና መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች አስታራቂነት ከአፈሩ ጋር “ሰላም” ፈጥረናል በማለት በዘይቤ ገለጣ አስረድተዋል።

በተለይ አቶ ሚሊዮን ዓለማየሁ የሚባሉት የወረዳው ግብርና ባለሙያ ያደረጉላቸውን ያላሰለሰ እርዳታ አድንቀው በተሰጣቸው ትምህርት በመታገዝ ጉድጓድ እየቆፈሩ ውሃ በማጠራቀም ካሮት፣ ድንች፣ ጎመንና ቀይ ሥር የመሳሰሉትን የጓሮ አትክልቶች በማምረት ተጠቃሚ መሆናቸውን አብራርተዋል።

አካባቢያቸውን ለማልማት ባላቸው ቁርጠኝነት ጊዜ በመወሰን የአካባቢውን ገበሬዎች በቀን ለሶስት ሰዓት ያህል እርከን በመሥራትና ውሃ የበላቸውን መሬቶች በማቅናት ባደረጉት የጋራ እንቅስቃሴ በአሁኑ ወቅት ምድረበዳ የነበረውን መሬት ደን ለብሶ ማየት እርካታ የሚሰጥ መሆኑን አስረድተዋል።



ሌላው የገበሬ ተወካይ የሰላሳ ስምንት ዓመቱ ጎልማሳ አቶ ታምሬ ሙሉነህ ናቸው። እኚህ ገበሬ ባደረጉት ንግግር አባታቸው ታታሪ ገበሬ ስለነበሩ ከእርሳቸው ጋር በመሥራት የእርከን ሥራ የሙያ ልምድ ገና በልጅነታቸው መቅሰማቸውንና ከዚያም በኋላ ተድረው አባታቸው ቆርጠው በሰጧቸው የእሸት መሬት

ላይ የግላቸውን የግብርና ሥራ እንደጀመሩ አብራርተዋል። በምሬቱ ላይ ካብ ከበው ጌሾ ከተከሉ በኋላ በመሃሉ ከባድ ውሃ ስለመጣ ባህርዛፍ፣ ጥጥ፣ ቡና፣ ፓፓያ፣ ጌሾ እንደተከሉ ገልጸዋል።

የሉተራን ድርጅት ተወካዮች ባደረጉላቸው ማበረታታትና በብድር መልክ በሰጧቸው ዘመናዊ ቀፎ በጀመሩት የንብ ማርባት ሥራ ሁለት ሳጥን ንብ በማስገባት ሰማንያ ኪሎ ማር እንዳመረቱና ማሩን በመሸጥ እዳቸውን ከመክፈላቸውም ሌላ የቀፎዎችን ቁጥር ወደ አሥራ ስምንት ከፍ አድርገው ሥራውን በማስፋፋት እንደቀጠሉ ገልጸዋል።

ከዚህ በኋላ ጥምር ግብርና ላይ ቢሰማሩ የተሻለ ጥቅም እንደሚያገኙ በተደረገላቸው ማበረታታት በጊቢያቸው ውስጥ የዶሮ እርባታ ሥራ ጀምረው የንብ መንጋ ዶሮዎቹን እንደጨረሱባቸው አስታውሰው ተስፋ ባለመቁረጥ የንብ ቀፎዎቹን ጫካ ወስደው በመስቀል የዶሮ እርባታውን ቀጥለው በአሁኑ ወቅት ሰላሳ ሁለት ዶሮዎች እንዳሏቸውና የቀፎዎቹም ቁጥር ሃያ ስድስት መድረሱን አስረድተዋል።

በዚህም ምክንያት ኑሮዋቸው ተሻሽሎ ልጆቻቸው ምንም ሳይጎድልባቸው እንደሚማሩ ገልጸዋል። የግብርና ሥራቸውን ቀን እየሰሩ በንብ እርባታ ሥራው ላይ የሚሰማሩት ወደማታ ስለሆነ የሥራ መደራረብ እንደሌለባቸውና የንብ እርባታ ስልጠና በአካባቢውም ለሚገኙ ሰላሳ ሁለት ገበሬዎች በማስተማር ተጠቃሚ ማድረጋቸውን አስረድተዋል። ለደረሱበት ደረጃ እግዚአብሔርን በማመስገን ንግግራቸውን ፈጽመዋል።

አቶ ሚሊዮን ዓለማየሁ ገበሬዎቹ በተናገሩት ላይ ጥቂት መጨመር እፈልጋለሁ በማለት እነሱ አጉልተው ባይናገሩትም ያደረጉትን ጥረት ከማበረታታት ያልዘለለ ሆኖም ከገበሬዎቹ ከራሳቸው ብዙ ነገር እንደተማሩ በማስረዳት ያላቸውን አስተያየት አክለዋል። በመጀመሪያ በአካባቢው ተመድበው ሲሰሩ የእነ ወ/ሮ አየለችን ዝና ሰሙ። ስለ ወ/ሮ አየለች ሰዎች ሲጠቅሱ "አየለች ያቺ ጎመኗ ጥሩ የሆነላት" ይላሉ። ከአፈር ጥበቃ ባሻገር ዘር መረጣና ማቆየት ጭምር እንደሚሰሩ ለመረዳት ቻሉ። ሥራቸውንም ካዩ በኋላ ተደንቀው ጠጋ ብለው ማጥናት እንደጀመሩና ፕሮጀክትም ቀርፀው ለበላይ አካላትና መንግሥታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች በማቅረብ ድጋፍ ለማግኘት እንደቻሉና በዚያው አካባቢ አንድ ምንጭ አጎልብተው የችግኝ ማፍያ ጣቢያ አቋቁመው መጠነኛ የሆነች የምርምር ሥራ መጀመራቸውን አስረድተዋል።

አቶ ሚሊዮን ባደረጉት ገለፃ ቀደም ሲል በዞኑ እርሻ ግምጃ ቤት ውስጥ አካፋና ዶማ ያለ ሥራ ተቀምጠው የነበረ ሲሆን ለገበሬዎቹ እንዲታደል ያደረጉትም ጥረት ባለመሳካቱ ኢ.ኤስ.አር.ዲ.ኤፍ (ESRDF) ለተባለ ድርጅት ጥያቄ አቅርበው በነአቶ ጌዲዮን አማካይነት አካፋና ዶማ ገዝተው ለ254 አባወራዎች አሰራጩ።

## የቪዲዮ ፊልም ትዕይንት

ከአቶ ሚሊዮን ዓለማየሁ ገለፃ በኋላ በአንኮበር ወረዳ አካባቢ የሚገኘውን የአካባቢ ሁኔታ ማለትም የመሬቱን አቀማመጥና የአፈር ጥበቃ አያያዝ የገበሬዎችንም የግልና የጋራ ጥረት የሚያሳይ የቪዲዮ ፊልም ታይቷል። ፊልሙ የተዘጋጀው የአሊዮአምባ አካባቢ በአልቶኬ ቀበሌ ገበሬ ማህበር ውስጥ ሲሆን በ1883 በአካባቢው ተጉዞ የነበረው አንድ እንግሊዛዊ ተጓዥ ቅጹ ህቀነበረው ሁኔታ የፃፈውን መነሻ በማድረግ ነው።

ከረጅም ዘመን በኋላ አፈሩ በጎርፍ ታጥቦ እንዳያልቅ እነ ወይዘሮ አየለች ፍቅሬ ባደረጉት የአፈር ጥበቃ ጥረት ከአንድ ሄክታር በማይበልጥ በማልማት ባህላዊው የአፈር ጥበቃ ዘዴ ከዘመናዊው የእርሻ ዘዴ ጋር በማቀናበር ከፍተኛ ለውጥ ማምጣት እንደሚቻል ከገለፃ ጋር ያሳያል። በተለይ ከወደላይ የሚወርደውን ፈሰስ ደለሉን በማስቀረትና ውሃውን መልሶ በመጠቀም ያካበቱት ልምድ ከፍተኛ ነው። "ሰው ይወለዳል መሬት ግን አይወለድም" የሚሉት ወ/ሮ አየለች ስለአፈር ጥበቃ አስፈላጊነት ያስረዳሉ። የአካባቢው ገበሬዎች ልዩ ልዩ አትክልቶችን፣ ፍራፍሬዎችንና የቅባት እህሎችን በማምረት የቀንድና የጋማ ከብቶችን በማርባት እንደዚሁም በጋራ የሚጠቀሙበት ከቤት ክዳን ጀምሮ ለልዩ ልዩ ጉዳይ የሚገለገሉበት ገመድ የሚሆን ጓሳ በመንከባከብ እንደሚተዳደሩ ፊልሙ ያብራራል።




ያካባቢው ዓይነተኛ ችግር በመርሓ ቤቴ የጀማ ወንዝን የመሳሰሉ ታላላቅ ወንዞች ዳርቻ ገመገም ከሚታረሰው መሬት አፈሩን በማጠብ የሚደርሱት የአፈር መከላት ችግር ነው። የፊልሙ አይነተኛ ዓላማ ሌሎችም ትምህርት እንዲያገኙበት በማሰብ የተሰራ ነው። ፊልሙ ታይቶ ካለቀ በኋላ ሰፋ ያለ ውይይት ተካሂዷል። ጥያቄና መልስ ተደርጎ አጥጋቢ ውይይት ተከናውኗል። ከውይይቱ በኋላ አቶ ግርማ አቅራቢዎቹን አመስግነው ወ/ሮ አየለች በቅርቡ ለከፍተኛ ሽልማት መብቃታቸውን አስታውቀው ተሳታፊዎችን በሙሉ ካመሰገኑ በኋላ የምሳ ዕረፍት ሆኗል።

## የፅዱና አረንጓድ አዲስ አበባ እንቅስቃሴ

ከተማይቱ ለነዋሪዎቿ ምቹ እንድትሆን የማድረግ ኃላፊነት ለመንግሥት ብቻ የሚተው ሳይሆን የሁሉም ጉዳይ ስለሆነ ከተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች የተውጣጡ ከ9 እስከ 11 አባላት የሚገኙበት ኮሚቴ ከሁለት ዓመት በፊት ተቋቁሞ በመንቀሳቀስ ላይ መሆኑንና ራዕዩም ምን እንደነበረና በሂደት የተደረገውን ለውጥና ወደ ፅዱና አረንጓዴ ማህበርነት መሸጋገሩን ዘርዝረው አብራሩ።

በዚህ ረገድ መንግሥት ሥራዬ ነው ብሎ ራሱን የቻለ ኤጀንሲ አቋቁሞ እንቅስቃሴ ጀምሯል። መዋቅሩንም የተለያዩ ባለሙያዎች በመመደብ ተግባራዊ እንቅስቃሴ እያካሄደ ይገኛል። ከተማዋ በአስር ክፍለ ከተማ መደራጀቷ ራሱን የቻለ ሌላ ተስፋ ነው ሲሉ ገልጸዋል። በመቀጠልም አዲስ አበባን ለማፅዳት የተለያዩ ደረጃዎች እንዳሉ ገልፀው በመጀመሪያ ከቀላል ተነስተን ወደ ከባድ መሄድ እንችላለን ብለዋል።

አያይዘውም ሲናገሩ ከተማዋ ፀዳች ማለት የሚቻለው ዋና ዋና ጎዳናዎችን በማፅዳት ብቻ አለመሆኑንና ወጪ ሳይበዛ ሕዝቡን በማስተባበር ጉራንጉሩን ሁሉ ማጽዳት እንደሚያስፈልግ ካለበለዚያ ግን ከላይ ንጹህ ሸሚዝ ለብሶ ከስር ቆሻሻ ካናቴራ እንደመልበስ ይቆጠራል ብለዋል። ሕዝቡ ቆሻሻ ምን ማለት እንደሆነ ከተማረና የአመለካከት ለውጥ ካዳበረ ያለ ብዙ ወጪ ከተማችንን ፅዱና አረንጓዴ ማድረግ እንችላለን ብለዋል። የማህበሩም ህጋዊነቱ እንዴት እየተጠናከረ እንደሚሄድ ከታች ከቀበሌ ደረጃ ጀምሮ ምን ዓይነት ኃላፊነት መውሰድ እንደሚገባ በሰፊው አስረድተዋል።

ከዚህ በኋላ ከሁለት የተለያዩ ዕድሮች የተወከሉ ሃላፊዎች ተሞክሮአቸውንና በአካባቢያቸው ስለሚያከናውኑት የአካባቢ ጥበቃና እንክብካቤ እንቅስቃሴ ሰፋ ያለ ገለጣ በየተራ ካቀረቡ በኋላ ስለወደፊቱ አቅጣጫና የማጠቃለያውን ሐሳብ አስተባባሪው አስተምረዋል።



## የት/ቤቶች የአካባቢ ጥበቃና እንክብካቤ ክበባት እንቅስቃሴ

የት/ቤቶችን የአካባቢ ጥበቃና እንክብካቤ እንቅስቃሴ በተመለከተ ለጉባዔው ሰፊ ማብራሪያ ያቀረቡት አቶ ብሩክ በቀለ ሲሆኑ እሳቸውም ባደረጉት ገለጻ በት/ቤቶች የሚደረጉ የአካባቢ ጥበቃና እንክብካቤ እንቅስቃሴዎች ዓላማና ግብ ተማሪዎች አካባቢያቸውን እንዴት መጠበቅ እንደሚችሉ ግንዛቤ እንዲያገኙና በትምህርት ቤትም ሆነ ከትምህርት ውጪ የቀሰሙትን ዕውቀት በተግባር እንዲተረጉሙ ነው። ይህ ዓላማ ካለፉት አስራ አምስት ዓመታት ጀምሮ በየትምህርት ቤቶች ውስጥ ልዩ ልዩ ክበባት በመመስረት ሥራ ላይ የዋለ መሆኑንና ሥራው የሚከናወነው ከሥራ ሰዓት ውጪ በክበቡ ለመሳተፍ ፈቃደኛ በሆኑ መምህራንና ተማሪዎች እንደሆነ አስረድተዋል።

በመቀጠልም ከክበቦች ሁሉ ከተፈጥሮ ጋር ቀጥታ ግንኙነት ያለውና እንቅስቃሴው በተጨባጭ የሚታየው የአካባቢ ጥበቃና እንክብካቤ ክበብ መሆኑን አስረድተው ለተማሪዎቹ በአካባቢ ጥበቃ ላይ ያተኮረ ትምህርቶች (ለምሳሌ የህዝብ ቁጥር መጨመር በአካባቢ ላይ ያለው ተፅዕኖ፣ የደን ጥቅምና አያያዝ፣ የአገር በቀል ዛፎች ጠቀሜታ፣ የአየርና የውሃ ብክለት የሚያስከትሉት ጉዳቶች ... ወዘተ) በመሳሰሉ ርዕሶች ላይ ጠቃሚ ትምህርቶች ይሰጣሉ ውይይቶችም ይካሄዳሉ። ተማሪዎቹ ከክፍል ውስጥ የሚያገኙትን ትምህርት በተግባር እንዲተረጉሙ ለማድረግ በየት/ቤቱ የችግኝ ተከላ እንቅስቃሴ፣ አትክልት ውሃ የማጠጣት ሥራ፣ የንብ እርባታ ሥራ፣ ወዘተ በተማሪዎች ይካሄዳል። ከማር ምርት እንደዚሁም ከአትክልትና ከችግኝ ሽያጭ በሚገኝ ገቢ የክበቡ አባላት ከአዲስ አበባ ውጪ ተጉዘው ትምህርታዊ ጉብኝት ያደርጋሉ። እንደዚሁም መንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር በመቀናጀት ተማሪዎች በየጊዜው በዛፍ ተከላ ላይ የሚሰማሩ መሆኑን በመግለጽ የት/ቤቶችን የአካባቢ ጥበቃ ክበቦች እንቅስቃሴ አቶ ብሩክ በዝርዝር አስረድተዋል። በመጨረሻም ተማሪዎች የሚያደርጉት እንቅስቃሴ ከተለያዩ ድርጅቶች በሚገኝ የገንዘብና የማቴሪያል ድጋፍ ስለሆነ ይህ ድጋፍ ሊቀጥል እንደሚገባ በማሳሰብ ንግግራቸውን አብቅተዋል።



## የወደፊት የእንቅስቃሴ አቅጣጫ

በስብሰባው ላይ በቀረቡት ፍሬ ሀሳቦች ላይ በመመርኮዝ የወደፊቱን የእንቅስቃሴ አቅጣጫ የሚጠቁም የማጠቃለያ አስተያየት የሰጡት አቶ ግርማ ኃይሉ ናቸው። አቶ ግርማ ባደረጉት ገለጻ ከስብሰባው ነጥረው የወጡ አራት ቁምነገሮች እንዳሉ አስረድተው በተቀዳሚነት የሚታየው በስፋት የሚገኙትን አገር በቀል እውቀቶች አስተካክሎና አሻሽሎ ሰዎች በቀላሉ በሚረዱት መልኩ አዘጋጅቶ የማስተላለፍ ሥራ ትኩረት ሊደረግበት የሚገባ መሆኑን ጠቅሰዋል። እነ ወ/ሮ አየለችን የመሳሰሉ ተመራማሪዎች ያፈለቋቸው እውቀቶች ተመዝግበው ለህብረተሰቡ የሚቀርቡበትን ዘዴ ማመቻቸት የሁሉም ዜጋ ጥረት መሆን እንዳለበት አቶ ግርማ አስምረውበታል። በአቶ ግርማም የቀረበው ሁለተኛ ሀሳብ "እነ ወ/ሮ አየለችን እንዴት ማስፋፋት ይቻላል" የሚል ነው። በአቶ ግርም አገላለጽ ወ/ሮ አየለች በአሁኑ ወቅት ግለሰብ ሳይሆኑ "ተቋም" ናቸው። ወ/ሮ አየለችና እርሳቸውን የመሳሰሉት የነበረውን አገር በቀል እውቀት እንደገና በሙከራ በማረጋገጥ ህይወት ሰጥተውታል ስለዚህ የእንደነ ወ/ሮ አየለች ዓይነቱን ተምሳሌቶች እንዴት አድርጎ ማባዛት ይቻላል? የሚለው የውይይቱ አንዱ ትልቅ ቁምነገር እንደሆነ አቶ ግርማ አብራርተዋል። አቶ ግርማ ያነሱት ሶስተኛ ነጥብ ከመኖሪያዎችና ከኢንዱስትሪ አካባቢዎች የሚወጡ ዝቃጮችና ደረቅ ቆሻሻዎች ጉዳይ ነው። እነዚህን ለአካባቢ ብክለት የሚዳርጉ ነገሮችን መኖር ከግንዛቤ ውስጥ ማስገባቱ ተገቢ ቢሆንም እነርሱን የልማት ግብአት አድርጎ በመጠቀም አካባቢን ለማሻሻል የሚደረገው ጥረት ልዩ ትኩረት ሊደረግበት እንደሚገባ ገልጸዋል።

በአራተኛ ደረጃ አቶ ግርማ ያነሱት ነጥብ ተባብሮ የመሥራትን አስፈላጊነት ነው። ህብረት፣ አቅምን፣ ገንዘብን፣ እውቀትን የሚያሰባስብ መሆኑን ገልጸው በተለይ በአዲስ አበባ አካባቢ የተሻሉ የኑሮ ሁኔታዎችን ለመፍጠር በተናጠል የሚንቀሳቀሱት ግለሰቦች መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በህብረትና በቅንጅት ሊንቀሳቀሱ እንደሚገባ ስብሰባው ትኩረት ካደረገባቸው ነጥቦች አንዱ መሆኑን አቶ ግርማ አስረድተዋል። እስካሁን ድረስ በጣም የተሳኩ ጅምሮች መኖራቸውና እነዚህ ጅምሮች እቅድ ከማውጣትና ከውይይት አልፈው ተግባራዊ እንዲሆኑና ስለተግባራዊነታቸውም ግምገማ ለማድረግ የሚቻልበት መድረክ መፍጠር ወሳኝ መሆኑን አቶ ግርማ አስተያየታቸውን አጠቃለዋል።

በመጨረሻም የተነሱትን የተለያዩ ነጥቦች በተመለከተ ሰፋ ያለ አጠቃላይ ውይይት ከተካሄደ በኋላ የዕለቱ ስብሰባ ተጠናቋል።

እነዚህ አራቱም ባሕሪያት ተመጣጥነው መገኘት ያለባቸው እጅግ አስፈላጊ የሆኑ እርስ በርሳቸው የሚጠባበቁ ነገሮች በመሆናቸው ሰዎች ለራሳቸውም ሆነ ሕይወት ላላቸው ነገሮች ሁሉ ከፍተኛ እንክብካቤ ሊያደርጉ ይገባል። ሰዎቹ እጽዋትን ሲጠብቁ እጽዋቶች ደግሞ ሰዎችን ይጠብቃሉ። የሰዎች ሕልውና በአካባቢ ደህንነት ላይ ይተመሰረተ መሆኑንና ምድር ከዕጽዋት ልብስ ከተገፈፈችና ከልምላሜ ጸጋ ከተራቆተች መልኳ እንደሚጠፋና ደረቅ እንደምትሆን ሕይወትንም እንደማታኖር በሰፊው አብራርተዋል። አዳምና ሔዋን በመጀመሪያ ገንት ውስጥ ሲፈጠሩ ዝም ብለው እንዲቀመጡ ሳይሆን እግዚአብሔር የሰጣቸውን የተፈጥሮ አካባቢ እንዲንከባከቡ ግዴታ የነበራቸው መሆኑንና ይህ ተግባር አሁንም መቀጠል እንዳለበት ቤተክርስቲያኒቷ የምታምንበት መሆኑን ገልጸው የምታደርገው እንቅስቃሴም በዚህ መርህ ላይ የተመረኮዘ እንደሆነ በመግለጽ መላእከ ሰላም ዳኛቸው ካሳሁን ስለ አካባቢ ጥበቃ ያላቸውን አስተያየት ገልጸዋል።




አንድ ገበሬ እርሻ ከመጀመሩ በፊት ጎተራውን እንደሚያዘጋጅ ሁሉ እግዚአብሔርም የሰውን ልጅ ከመፍጠሩ በፊት አዳም ከነዘሩ እንዳይቸገር ሁሉንም ነገር አስቀድሞ ፈጠረለት። በመጨረሻም በገነት ውስጥ አስቀመጠው። ገነት በአረንጓዴ ዕጽዋትና በለመለመው ዛፎች። እንዲሁም በምንጮችና ፏፏቴዎች የተሞላች ውብና ድንቅ ሥፍራ መሆኗ ተጽፏል። የሰው ልጅ የተፈጠረለትን ገነት ተንከባክቦ እንዲይዝና እንዲሰራባት እንጂ እጁን አጥፎ እንዲቀመጥ አይደለም በማለት አስረድተዋል። በዚህ መሰረት አካባቢውን ለመኖሪያ እንድትሆን ተንከባክቦ መያዝ እንደሚገባውና ኃላፊነትም እንዳለበት አስገንዝበዋል።

ከዚህ በኋላ የሻይ ዕረፍት ተደርጎ አቶ ግርማ ሀይሉ እያንዳንዱ ተናጋሪ ካቀረበው ጠቃሚና ዋና ዋና የሆኑትን ፍሬ ሃሳቦች በማጠቃለል ስለወደፊቱ አቅጣጫ የሚከተለውን አጠር ያለ ማጠቃለያ ሰጥተዋል።

## የአዲስ አበባ የጽዳት፣ ውበትና መናፈሻ ልማት

የጽዱና አረንጓዴ አዲስ አበባን እንክብካቤ በተመለከተ ገለጣ የሰጡት አቶ ፍቅሩ አበበ ሲሆኑ መናፈሻዎችንም በተመለከተ አቶ ከበደ ፋሪስ ሰፋ ያለና ጠቃሚ ንግግር አድርገዋል። አቶ ፍቅሩ ባደረጉት ንግግር አዲስ አበባ ባሁኑ ጊዜ የአገሪቱ ዋና ከተማ ብቻ ሳትሆን የአፍሪካ ሕብረትም መዲና እንደመሆኗ ጽዱና አረንጓዴ መሆን ይጠበቅባታል በማለት በሰፊው አስረድተዋል።



## የቤተ ክህነት የዕጽዋት ጥበቃና እንክብካቤ

ርዕሱን አስመልክተው ለጉባዔው ንግግር ያደረጉት መልአከ ሰላም ዳኛቸው ካሳሁን ናቸው። እርሳቸውም ባደረጉት ገለጻ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ዙሪያ ዛፎችንና ዕጽዋትን ለምን እንደምትተክልና ቀደም ሲል የተተከሉትን የምትጠብቅበት ምክንያት ምን እንደሆነ፣ በአሁኑ ወቅት በአድባራትና በገዳማት ዙሪያ የሚገኙ ዛፎች በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኙ፣ አካባቢ መጠበቅን በተመለከተ ቤተክርስቲያኒቷ ምን ሥራ እየሰራች እንደሆነና የወደፊት እቅዷ ምን እንደሚ መስል በዝርዝር አብራርተዋል። አስተያየታቸውን ጠቅለል አድርገው ሲያቀርቡ በቤተክርስቲያኒቷ አገላለጽ የሥጋ ባህሪያት ተብለው የተሰጡ አራት ባህሪያት መኖራቸውንና እነርሱም እሳት፣ ውሃ፣ ነፋስና መሬት መሆናቸውን አስረድተው እነዚህ ባህሪያት በሰው ልጆችና በእጽዋትም ላይ ተመሳሳይ እንደሆኑ ገልጸው ተመጣጥነው ካልተገኙ ወይም ደግሞ አንዱ ቢጎድል ህይወት እንደማይኖር ዕጽዋትም እንደማያድጉ፣ እንደማይ ለመልሙና እንደማያብቡ ያለውን እምነት በዝርዝር አስረድተዋል።

# FSS PUBLICATION LIST

## FSS Newsletter

*Medrek, now renamed BULLETIN* (Quarterly since 1998. English and Amharic)

## FSS Discussion Papers

No.1. *Water Resource Development in Ethiopia: Issues of Sustainability and Participation*. Dessalegn Rahmato. June 1999

No. 2. *The City of Addis Ababa: Policy Options for the Governance and Management of a City with Multiple Identity*. Meheret Ayenew. December 1999

No. 3. *Listening to the Poor: A Study Based on Selected Rural and Urban Sites in Ethiopia*. Aklilu Kidanu and Dessalegn Rahmato. May 2000

No. 4. *Small-Scale Irrigation and Household Food Security: A Case Study from Central Ethiopia*. FuadAdem. February 2001

No. 5. *Land Redistribution and Female-Headed Households*. Yirgemew Adal. November 2001

No. 6. *Environmental Impact of Development Policies in Peripheral Areas: The Case of Metekel, Northwest Ethiopia.* Wolde-Selassie Abbute. Forthcoming, 2001

No. 7. *The Environmental Impact of Small-Scale Irrigation: A Case Study.* Fuad Adem. Forthcoming, 2001

No. 8. *Livelihood Insecurity Among Urban Households in Ethiopia.* Dessalegn Rahmato and Aklilu Kidanu. October 2002

No. 9. *Rural Poverty in Ethiopia: Household Case Studies from North Shewa.* Yared Amare. December 2002

No. 10. *Rural Lands in Ethiopia: Issues, Evidences and Policy Response.* Tesfaye Teklu. May 2003

No. 11. *Resettlement in Ethiopia: The Tragedy of Population Relocation in the 1980s.* Dessalegn Rahmato. June 2003

## FSS Monograph Series

No. 1. *Survey of the Private Press in Ethiopia: 1991-1999.* Shimelis Bonsa. 2000

No. 2. *Environmental Change and State Policy in Ethiopia: Lessons from Past Experience.* Dessalegn Rahmato. 2001

No. 3. *Democratic Assistance to Post-Conflict Ethiopia: Impact and Limitations.* Dessalegn Rahmato and Meheret Ayenew. 2004

## FSS Conference Proceedings

1. *Issues in Rural Development. Proceedings of the Inaugural Workshop of the Forum for Social Studies, 18 September 1998.* Edited by Zenebework Tadesse. 2000
2. *Development and Public Access to Information in Ethiopia.* Edited by Zenebework Tadesse. 2000
3. *Environment and Development in Ethiopia.* Edited by Zenebework Tadesse. 2001
4. *Food Security and Sustainable Livelihoods in Ethiopia.* Edited by Yared Amare. 2001
5. *Natural Resource Management in Ethiopia.* Edited by Alula Pankhurst. 2001
6. *Poverty and Poverty Policy in Ethiopia.* Special issue containing the parers of FSS' final conference on poverty held on 8 March 2002

## Consultation Papers on Poverty

No. 1. *The Social Dimensions of Poverty.* Papers by Minas Hiruy, Abebe Kebede, and Zenebework Tadesse. Edited by Meheret Ayenew. June 2001

No. 2. *NGOs and Poverty Reduction.* Papers by Fassil W. Mariam, Abowork Haile, Berhanu Geleto, and Jemal Ahmed. Edited by Meheret Ayenew. July 2001

No. 3. *Civil Society Groups and Poverty Reduction.* Papers by Abonesh H. Mariam, Zena Berhanu, and Zewdie Shitie. Edited by Meheret Ayenew. August 2001

No. 4. *Listening to the Poor. (Amharic).* Oral Presentation by Gizachew Haile, Senait Zenawi, Sisay Gessesse and Martha Tadesse. Edited by Meheret Ayenew. November 2001

No. 5. *The Private Sector and Poverty Reduction (Amharic).* Papers by Teshome Kebede, Mullu Solomon and Hailemeskel Abebe. Edited by Meheret Ayenew, November 2001

No. 6. *Government, Donors and Poverty Reduction.* Papers by H.E. Ato Mekonnen Manyazewal, William James Smith and Jeroen Verheul. Edited by Meheret Ayenew, February 2002.

No. 7. *Poverty and Poverty Policy in Ethiopia.* Edited by Meheret Ayenew, 2002

## Books

1. *Ethiopia: The Challenge of Democracy from Below.* Edited by Bahru Zewde and Siegfried Pausewang. Nordic African Institute, Uppsala and the Forum for Social Studies, Addis Ababa. 2002

## Special Publications

*Thematic Briefings on Natural Resource Management, Enlarged Edition.* Edited by Alula Pankhurst. Produced jointly by the Forum for Social Studies and the University of Sussex. January 2001

## New Series

- **Gender Policy Dialogue Series**

No. 1. *Gender and Economic Policy.* Edited by Zenebework Tadesse. March 2003
No. 2. *Gender and Poverty (Amharic).* Edited by Zenebework Tadesse. March 2003
No. 3. *Gender and Social Development in Ethiopia.* (Forthcoming).
No. 4. *Gender Policy Dialogue in Oromiya Region.* Edited by Eshetu Bekele. September 2003

- **Consultation Papers on Environment**

No. 1. *Environment and Environmental Change in Ethiopia.* Edited by Gedion Asfaw. Consultation Papers on Environment. March 2003
No. 2. *Environment, Poverty and Gender.* Edited by Gedion Asfaw. Consultation Papers on Environment. May 2003
No. 3. *Environmental Conflict.* Edited by Gedion Asfaw. Consultation Papers on Environment. July 2003
No. 4. *Economic Development and its Environmental Impact.* Edited by Gedion Asfaw. Consultation Papers on Environment. August 2003
No. 5. *Government and Environmental Policy.* Consultation Papers on Environment. January 2004

- **FSS Studies on Poverty**

No. 1. *Some Aspects of Poverty in Ethiopia: Three Selected Papers.* Papers by Dessalegn Rahmato, Meheret Ayenew and Aklilu Kidanu. Edited by Dessalegn Rahmato. March 2003
No. 2. *Faces of Poverty: Life in Gäta, Wälo.* By Harald Aspen. June 2003
No. 3. *Destitution in Rural Ethiopia.* By Yared Amare. Ausust 2003